የሰ/መ/ቁ. 38181

ግንቦት 4 ቀን 2001 ዓ.ም

**ዳኞች፡-** ዓብዱልቃድር መሐመድ

ሐጎስ ወልዱ

ሒሩት መለሠ

በላቸው አንሺሶ

ሱልጣን አባተማም

**አመልካች፡-** የኢት/መንገዶች ባለሥልጣን - ነ/ፈጅ ጌታቸው አካሣ ቀረቡ፡፡

**ተጠሪዎች፡-** 1. ወ/ሮ ትዕግሥት ወንድይፍራው - ጠ/ላቀ ቀረቡ፡፡

2. አቶ ባህሩ አህመድ - በሌሉበት

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ጉዳይ ክስ በሚሠማበት ቀጠሮ የከሣሽ /የይግባኝ ባይ/ አለመቅረብ የሚያስከትለውን ውጤት የሚመለከት ነው፡፡

ጉዳዩ የተጀመረው በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ሲሆን አመልካች ከሣሽ ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ ተከሣሾች ነበሩ፡፡ በክሱም የአንደኛ ተጠሪ ንብረት የሆነውን መኪና ሁለተኛ ተጠሪ ሲያሽከረክሩ በግልገል ግቤ ወንዝ ላይ የተሠራው ድልድይ ላይ ጉዳት በማድረሣቸው ተጠሪዎች ለደረሰው ጉዳት ካሣ እንዲከፍሉ ጠይቋል፡፡ ፍ/ቤቱም ግራ ቀኙን አከራክሮ የከሣሽን ክስ ውድቅ በማድረግ ወስኗል፡፡ በዚህ ውሣኔ ላይ አመልካች በፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት የይግባኝ ቅሬታውን ያቀረበ ሲሆን የይግባኝ ቅሬታው መልስ ሰጪዎች ባሉበት የሚጣራ ነጥብ በማግኘቱ ይግባኙን ለመስማት ቀጠሮ ሠጥቷል፡፡

ይግባኙ በሚሠማበት ዕለትም አመልካች ባለመቅረቡና የአንደኛ ተጠሪ ጠበቃም መዝገቡ እንዲዘጋላቸው ስለጠየቁ ፍ/ቤት መዝገቡን በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት ዘግቷል፡፡ አመልካች የተዘጋው መዝገብ እንዲንቀሳቀስ እንዲፈቀድ አመልክቶ ፍ/ቤቱ በቂ ምክንያት አልቀረበም በሚል ጥያቄውን ሣይቀበለው ቀርቷል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚህ ውሣኔ ላይ ነው፡፡ በቅሬታውም አንደኛ ተጠሪ የተከሠሠበትን ነገር ሣይክድ መዝገቡ እንዲዘጋ በመጠየቁ ብቻ መዘጋቱ ስህተት ነው፤ ለሁለተኛ ተጠሪ መጥሪያ መስጠት እንዳልተቻለ ለፍ/ቤቱ ተገልፆ የርሣቸው ጥሪ ጉዳይ በእንጥልጥል ላይ እያለ ጉዳዩን ለመስማት የሚያስችል ሁኔታ ሣይኖርና ሁለተኛ ተጠሪ በምትክ መጥሪያ ሣይጠሩ መዝገቡ መዘጋቱ ስህተት ነው፤ በቀጠሮው እለት ያልቀረብንበት በቂ ምክንያት እያለ መታለፉ ስህተት ነው፤ በማለት የሥር ፍ/ቤት ውሣኔ ተሽሮ መዝገቡ ተከፍቶ እንዲታይ አመልክቷል፡፡

ይህ ችሎትም መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት የመዘጋቱን አግባብነት ለመመርመር አቤቱታው ለሰበር ችሎት ያስቀርባል በማለቱ ተጠሪዎች እንዲቀርቡ ታዘው ሁለተኛ ተጠሪ አልቀረቡም፡፡ አንደኛ ተጠሪ ቀርበው የግራ ቀኙ የቃል ክርክር ተሠምቷል፡፡ ከፍ ሲል የተገለፀው የግራ ቀኙ ክርክር ሲሆን ችሎቱም መዝገቡን እንደሚከተለው መርምሯል፡፡ በዚህ ጉዳይ ሊመለስ የሚገባው የይግባኝ ቅሬታው በሚሰማበት ቀን ይግባኝ ባይ /የአሁን አመልካች/ ያልቀረበ ቢሆንም አንደኛ ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታውን ክደው ሣይከራከሩ መዝገቡ መዘጋቱ በአግባቡ ነው አይደለም? የሚለው ነጥብ ነው፡፡

ስለ ባለጉዳዮች ፍ/ቤት መቅረብና ሣይቀርቡ መቅረት በሚናገረው ምዕራፍ ውስጥ የሚገኘው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ ቁጥር 73 ባንድ ነገር ክስ ያቀረበ ሰው ክርክሩ እንዲሰማ በተወሰነው ቀን ቀጠሮ ሣይቀርብ የቀረ እንደሆነ ተከሣሹ ቀርቦ

የተከሠሠበትን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ያመነ እንደሆነ ከሣሹ በሌለበትም ቢሆን ፍ/ቤቱ ተከሣሽ ላመነው ጉዳይ ውሣኔ መስጠት እንደሚችል ተከሳሹ የካደ እንደሆነ ግን መዝገቡን እንደሚዘጋውና ተከሣሹን እንደሚያሠናብት ይደነግጋል፡፡ በእርግጥ ይህ ድንጋጌ ከሣሽና ተከሣሽ እያለ የሚናገር ይሁን እንጂ የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕጉ በይግባኝ የሚቀርቡትንም ክርክሮች አጠቃሎ ስለሚይዝ እንደነገሩ አግባብ ከሣሽ የሚለው ቃል ይግባኝ ባይን ተከሣሽ የሚለው ደግሞ መ/ሰጪን የሚተካ ስለመሆኑ በዚሁ ሕግ ቁጥር 32/2/ ሥር ተመልክቷል፡፡ በመሆኑም የይግባኝ ቅሬታው በሚሠማበት ቀነ ቀጠሮ ይግባኝ ባይ ካልቀረበ ተፈፃሚነት ያለው ይኸው የፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 ነው፡፡ በዚህ የሥነ ሥርዓቱ ድንጋጌ ደግሞ ይግባኙ በሚሠማበት ቀነ ቀጠሮ ይግባኝ ባይ ያልቀረበ ከሆነ መ/ሰጪው ይግባኝ የቀረበበትን ነጥብ በከፊል ወይም በሙሉ ካመነ በእምነቱ መሠረት ፍ/ቤቱ ውሣኔ የሚሠጥ መሆኑን ነገር ግን ይግባኙን ክዶ የተከራከረ ከሆነ መዝገቡን መዝጋት እንዳለበት ተመልክቷል፡፡ በዚህም መሠረት የይግባኙ መዝገብ መዘጋት የሚወሰነው መ/ሰጪው ለቀረበበት የይግባኝ ቅሬታ ከሚሠጠው መልስ አኳያ ታይቶ ነው ማለት ነው፡፡ በመሆኑም መ/ሰጪ የቀረበውን የይግባኝ ቅሬታ መካድ ማመኑ ሣይረጋገጥ መዝገቡ እንዲዘጋ በመጠየቁ ብቻ መዝገቡ ሊዘጋ የሚችልበትን ሁኔታ ድንጌጋው አያመለክትም፡፡ በመሆኑም የይግባኝ ሠሚው ፍ/ቤት የአንደኛ መልስ ሰጪን መልስ ሣይመለከት መዝገቡን መዝጋቱ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

በሌላ በኩል ከአመልካች አቤቱታ እንደተመለከትነው ሁለተኛ ተጠሪ በይግባኝ ሰሚ ፍ/ቤት እንዲቀርቡ የተላከላቸውን መጥሪያ መ/ሰጪውን አግኝቶ መስጠት አለመቻሉ ለፍ/ቤቱ ተገልፆለት ሁለተኛ ተጠሪ እንዲቀርቡ ምትክ መጥሪያ ሳይላክ በእንጥልጥል ላይ የነበረ መሆኑን ተረድተናል፡፡ ሁለተኛ ተጠሪ በዚህ ፍ/ቤትም ተጠርተው ያልቀረቡ በመሆኑ በዚህ ነጥብ ላይ የቀረበ ማስተባበያ የለም፡፡ በመሆኑም ሁለተኛ ተጠሪ በምትክ መጥሪያ እንዲጠሩ ፍ/ቤት ትዕዛዝ ሣይሠጥ አመልካች ይግባኝ በሚሠማበት ቀን አልቀረበም በማለት በሁለተኛ ተጠሪ ላይ የቀረበውን ይግባኝም አብሮ መዘጋቱ አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

በአጠቃላይ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት መዝገብ የሚዘጋው ይግባኝ ባዩ የይግባኝ ቅሬታውን ክዶ ከተከራከረ በመሆኑ የአንደኛ ይግባኝ ባይ መልስ ተጠይቆ ሳይረጋገጥ መዝገቡ መዘጋቱም ሆነ ለሁለተኛ ተጠሪ መድረስ አለመቻሉ ተገልፆ ሳለ በምትክ መጥሪያ እንዲቀርብ ሣይታዘዝ መዝገቡ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 73 መሠረት መዘጋቱ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/ጠቅላይ ፍ/ቤት በመ/ቁ. 33199 ግንቦት 5/2000 ዓ.ም. እንዲሁም በዚህ መዝገብ ግንቦት 14/2000 ዓ.ም. የሰጠው ትዕዛዝ ተሽሯል፡፡
2. የተዘጋው መዝገብ ተከፍቶ ነገሩ እንዲቀጥል ብለናል፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡ መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ለመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ